# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1994 በጀት ዓመት
## የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1994

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1994 በጀት ዓመት
## የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1994

# ማ ው ጫ

**አርዕስት** **ገጽ**

1. መግቢያ------------------------------------------------------------1

2. የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ------------------------------------------------------------3
   2.1 የሥነ-ሕዝብና ጤና (DHS) በተመለከተ------------------------------------------------------------3
   2.2 የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ የምርምር ውጤቶች ማስታወቂያ ሲሚናር------3
   2.3 የ1997 ዓ.ም አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅትን በተመለከተ---------------4
   2.4 የቫይታል ስታቲስቲክስ በተመለከተ------------------------------------------------------------5
   2.5 የልጆች የስራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ------------------------------------------------------------6
   2.6 የማሕበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ------------------------------------------------------------7
   2.7 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት------------------------------------------------------------8

3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ------------------------------------------------------------8
   3.1 የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት------------------------------------------------------------8
   3.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት------------------------------------------------------------13
   3.3 የኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት------------------------15

4. የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ------------------------------------------------------------17
   4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በተመለከተ------------------------------------------------------------18
   4.2 የካርቶግራፊና የመዛግብት አያያዝ በተመለከተ------------------------------------------------------------18

5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ------------------------------------------------------------19
6. ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት------------------------------------------------------------20
7. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት------------------------------------------------------------20
8. የሥራ አመራርና ሥልጠና አገልግሎት------------------------------------------------------------23
9. የሕግ አገልግሎት------------------------------------------------------------22
10. የኦዲት አገልግሎት ------------------------------------------------------------ 23
11. የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት------------------------------------------------------------24

12. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና.------------------------------------------------------------25
   12.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ------------------------------------------------------------25
   12.2 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ------------------------------------------------------------26

13. የበጀት አጠቃቀም------------------------------------------------------------28
   ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም------------------------------------------------------------28
   ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም------------------------------------------------------------29

14. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት ------------------------------------------------------------32
   14.1 የዕቃ ግዢን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎች ------------------------------------------------------------32
   14.2 ትራንስፖርትና ጥገናን በተመለከተ------------------------------------------------------------33
   14.3 ሕትመት------------------------------------------------------------33

15. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ------------------------------------------------------------34

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
# የ1994 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት ባለፉት ሦስት አስርት ዓመታት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ ነክ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር፣ በመገምገም፣ በመተንተንና ሪፖርት በማዘጋጀት ለመንግሥትና ለሌሎች የመረጃ ተጠቃሚዎች ያሰራጨ ሲሆን፤ አሁንም በማሰራጨት ላይ ይገኛል። እነዚህን ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ለማዘጋጀት ከመንግሥትና ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በየጊዜው በርካታ የገንዘብ፣ የቁሣቁስና የሙያ ድጋፍ ለባለሥልጣኑ መ/ቤት የተሰጠ ሲሆን፤ የጥናቶቹም ይዘትና የጥራት ደረጃ እያደገና ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟሉ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

በ1994 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት በሁለት ፕሮጀክቶች ስር የሚካሄዱ በርካታ ጥናቶችን በዕቅድ ይዞ ያከናወነ ሲሆን፤ በተለይም በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ አብይና በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የሚፈለገውን የመረጃ ዓይነት በስፋትና በጥልቀት የሚዳስስና በዘርፉ ያለውን የመረጃ ክፍተት ያሟላል ተብሎ በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ነው። በመሆኑም በዚህ ቆጠራ በአገሪቱ የሚገኙ ሁሉም ወረዳዎችና በናሙና በተመረጡ በገጠር 11,199 እና በከተማ 4,100 በድምሩ 15,299 የቆጠራ ቦታዎች እንደዚሁም በበርካታ የመንግሥት የግል ንግድና የድርጅት እርሻዎች ተሸፍነዋል። ሆኖም በሱማሌና በአፋር ብሔራዊ ክልል በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች ይህ ሥራ አልተካሄደም። የግብርና ናሙና ቆጠራውን ለማስፈጸም ከ131 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት፣ በርካታ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ከመንግሥት ተመድቧል።

የባለሥልጣኑ መ/ቤት ይህን አዲስ ተግባር በጥራትና በተፈለገው መንገድ ለማከናወን በስሩ በነበሩት ነባር 22 ቅ/ጽ/ቤቶች በተጨማሪ እንደሥራው ክብደትና ስፋት 25 አዳዲስ የቆጠራ ጽ/ቤቶችን በመላው አገሪቱ በመክፈት በሰው ኃይልና በሎጅስቲክስ በማሟላት የግብርና ናሙና ቆጠራውን ሥራ በበላይነት እንዲያስተባብሩና በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም አድርገዋል። በዚህም ቆጠራ በተሸፈኑ አካባቢዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በወጣላቸው መረሃ ግብር መሠረት በወቅቱ እንዲሰበሰቡና የቆጠራ ዶክመንቶች ወደዋናው መ/ቤት እንዲመጡ በማድረግ ከፍተኛ ተግባር ፈጽመዋል።

በ1994 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ለስታቲስቲክስ መረጃ ሃብት መጎልበት አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ አስር ልዩ ልዩ ጥናቶችንና በ1993 ዓ.ም የተጀመሩ ሁለት ጥናቶችን የሪፖርት ዝግጅታቸውን ለማጠናቀቅ አቅዶ ነበር፡፡ እነዚህም ጥናቶች፡-

ሀ. የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣
- የግብርና የገጠር የግል ባለይዞታዎች ቆጠራ (የመኸርና የበልግ፣ የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች ቆጠራ)፣
- የከተማ አካባቢ የግብርና ቆጠራ፣
- የሰፋፊና መካከለኛ የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች ቆጠራ፣ እና
- የአርብቶ አደር አካባቢ የግብርና ቆጠራ፣

ለ. የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም

- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት፣
- በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣
- የመካከለኛ፣ የትላልቅና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
- የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባ ጥናት፣ እና
- የዋጋዎች ኢንዴክስ ዝግጅት፣

ሐ. በ1993 ዓ.ም የተጀመሩና በዕቅድ ዓመቱ የሚጠናቀቁ የጥናት ሪፖርቶች

- የመካከለኛ፣ የትላልቅና የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ እና
- የሕፃናት ሥራ ሁኔታ ጥናት ( Stand - alone Child Labour Survey)፣ ናቸው፡፡

መ/ቤቱ ባለው የሰው ኃይል በመንግሥትና በውጪ ዕርዳታ ባገኘው የበጀትና የቁሣቁስ ድጋፍ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ከላይ የተዘረዘሩትን ጥናቶች በማካሄድና በማጠናቀቅ ረገድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደረገ ሲሆን፣ የተከናወኑት ዋና ዋና ተግባራቱም በዚህ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ከዚህም ጋር የሰው ኃይል ሁኔታ፣ የፋይናንስ አጠቃቀምና ሌሎችም አኀዛዊ መግለጫዎች በሪፖርቱ ተጠቃለዋል፡፡ እንደዚሁም በበጀት ዓመቱ ውስጥ በዕቅድ አፈፃፀሙ ላይ የታዩ ችግሮችና መ/ቤቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት መወጣት ይችል ዘንድ ለቀጣዩ የበጀት ዓመት በበላይ አካል ትኩረት ተሰጥቶአቸው ከወዲሁ መፍትሄ የሚሹ አጠቃላይ ችግሮች በሪፖርቱ መጨረሻ ክፍል እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## 2. <u>የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስ</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት  በየዘርፉ ያለውን የመረጃ ክፍተት ደረጃ በደረጃ ለማጥበብ ከሚያሂዳቸው ጥናቶች ውስጥ የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ የተለያዩ ሕዝብ ነክ ጥናቶች ዋነኞቹ ናቸው። በዘርፉ ያለውን የመረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ ከተካሄዱት ሁለቱ ብሔራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራዎች በተጨማሪ ሌሎች ጥናቶችንም በማካሄድ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጩ አድርጓል። በ1994 በጀት ዓመት የሕዝብና ቤት ስታቲስቲክስን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት የባለሥልጣኑ መ/ቤት አከናውኗል።

### 2.1 <u>የሥነ - ሕዝብና ጤና ጥናትን (DHS) በተመለከተ</u>

<u>የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት ዋናውን ሪፖርት ለክልሎች ማስተዋወቂያ ሴሚናር ዝግጅት</u>

የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት ዋናው ሪፖርት በአገር አቀፍ ደረጃ የአንድ ቀን የማስተዋወቂያ ሴሚናር በ1993 በጀት መጨረሻ ላይ መካሄዱ ይታወቃል። ይህንኑ ሪፖርት በ1994 በጀት ዓመት በተመሣሣይ ሁኔታ በሁሉም ክልሎች፣ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ አስተዳደሮች የማስተዋወቂያ ዓውደ ጥናት የተካሄደ ሲሆን፣ ዓውደ ጥናቱ በተካሄደባቸው ክልሎችና አስተዳደሮች ላይ የተዘጋጁ ሪፖርቶችና የ"Power Point" ጽሑፎች ተዘጋጅተው ለሴሚናሩ ተካፋዬች ቀርበዋል። በየክልሎቹ የተካሄዱት እነዚህ ሴሚናሮች ከክልሎቹ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር ነው።

### 2.2 <u>የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዎች ዝርዝርና ጥልቀት ያለው የምርምር ጽሑፎች ማስተዋወቂያ ሴሚናር፣</u>

በበጀት ዓመቱ ከጣሊያን አገር ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች፣ የምርምር ተቋማትና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከሚገኘው የሥነ - ሕዝብ ማሠልጠኛ ማዕከል ጋር በመተባበር የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ሰባት ዝርዝርና ጥልቀት ያለው የምርምር ጽሑፎችን በማዘጋጀት የአንድ ቀን የማስተዋወቂያ ሴሚናር በአዲስ አበባ የተባበሩት መንግሥታት የስብሰባ ማዕከል አካሂዷል።  በስብሰባው ከጣሊያን አገር የመጡ ምሁራንና የመ/ቤቱ ባልደረቦች ጽሑፎችን በማቅረብ የተሳተፉ ሲሆን፣ በሴሚናሩ ወደ 100 የሚጠጉ በመስኩ የተሰማሩ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል። በውይይቱ ሂደት ከተሳታፊዎች የቀረቡትን አስተያየቶች በማካተት ሰባቱ ሪፖርቶች ተጠናቀውና ታትመው በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለሚገኙ  የምርምር ተቋማትና ቤተመፃሕፍት እንዲሁም ለሌሎች ለተጠቃሚዎች ተሠራጭተዋል።

## 2.3 የ1997 አጠቃላይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዝግጅት

- በ1997 ዓ.ም ሊካሄድ ለታሰበው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ተግባር በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ አብዛኛው ሥራ በቅድመ ቆጠራ የካርታ ሥራ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የካርታ ሥራው ሰፊ የሆነ ገንዘብና የሰው ኃይል የሚሣተፍበት ሲሆን፤ በአገሪቱ የሚገኙትን ቀበሌዎችና መንደሮች እንዲሁም ቤቶችን ሁሉ በመጎብኘት የቆጠራ ካርታ ሥራ ይካሄዳል፡፡ በዚህ መጠነ ሰፊ የካርታ ሥራ ወቅት የሚገኘውን መረጃ በስፋት ጥቅም ላይ ለማዋል የካርታ ሥራውን ኮምፒዩተራይዝ ለማድረግ ኮምፒውተሮች፣ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች፣ ዲጂታይዘሮች፣ ስካነሮች፣ ፕሎተሮችና ትላልቅ ከለር ፕሪንተሮች ከውጪ አገር በUNFPA ዕርዳታ ታዝው አብዛኛዎቹን ርክክብ ተፈፅሟል፡፡ በተጨማሪም ለካርታ ሥራው መገዛት ያለባቸው GPS, Plan Printer, Digital area Calculator, Lettering System, Drawing Sets, Drawing Pens, Tracing Paper, ፎቶ ኮፒየሮች…ወዘተ ከውጪ አገር በUNFPA በኩል እንዲገዙ የተደረገ ሲሆን ርክክብ ተከናውኗል፡፡

- በ1997 ለሚካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ አገልግሎት የሚውሉ ካርታዎችን በኮምፒውተር ለማዘጋጀት መ/ቤቱ ባሠለጠናቸው ባለሙያዎች አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት እየተካሄደ ሲሆን፤ በተለይም የካርታ ሥራውን ለማካሄድ የሚያገለግለውን መመሪያ በማዘጋጀት የመጀመሪያው ድራፍት ለሁለት ቀናት በመስክ ሙከራ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ማሻሻያዎችንና ለውጦችን በመጀመሪያው ድራፍት ላይ በማካተት ለሁለተኛ ጊዜ ተመሣሣይ የመስክ ሙከራ ተደርጎ መመሪያው የመጨረሻ መልኩን የያዘ ሲሆን፤ መመሪያውን ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የመተርጎም ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

- ለካርታ ሥራው የመስክ ሥራና ለዋናው ቆጠራ ጭምር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ዝርዝርና አጠቃላይ የፕሮጀክት ዶክመንት ከUNFPA CST ከተመደ ባለሙያ ጋር በመተባበር ሪፖርት የተዘጋጀ ሲሆን፤ ፕሮጀክት ዶክመንቱም ለዕርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች ሁሉ እንዲደርስና አስፈላጊው ዕርዳታ እንዲገኝ ለማድረግ ይሠራሜል፡፡

- የUNFPA አራተኛው ዙር የዕርዳታ ፕሮግራም በ Dec.2001 ስለተጠናቀቀ ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት የሚያገለግል የዕርዳታ ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡ ለቀጣዩ ዙር ፕሮግራም ዝግጅትም መ/ቤቱ በአባልነት ተወክሎ ሠርቷል፡፡

## 2.4 የቫይታል ስታቲስቲክስ በተመለከተ

- የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲካል የሙከራ የጥናት ቦታዎችን ለመፍጠርም ሆነ ከአስፈፃሚ ተቋማቱ ጋር ለመሥራት የሚያስችሉ የአሠራር ስልቶችን የሚገልጽ " በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለማቋቋም የተዘጋጀ ዕቅድና አፈፃፀም ስልት ረቂቅ" ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም የዚሁ ስታቲስቲክስ የመዝጋቢዎች መመሪያ ሰስተኛ ረቂቅ ለአስተያየት የቀረበ ሲሆን፣ መመሪያው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቅጾችን ይዘት፣ የምስክር ወረቀቶችንና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሪፖርት ቅጾችን የያዘ ነው፡፡

- ከምዝገባውና ከወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ቅጾች ላይ ሊጠናቀሩ የሚችሉ ዝርዝር የመረጃ ሠንጠረዦች (Proposed List of Tables) በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅተዋል፡፡

- በመ/ቤቱ ለሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኤክስፐርቶችና ቴክኒሽያኖች በተዘጋጁት የመዝጋቢዎች መመሪያ፣ የዕቅድና አፈፃፀም ስልት፣ እንዲሁም ስለ " Civil registration" እና Vital statistics" ጥልቅ ሥልጠናና የመማሚሪያ መድረክ በማዘጋጀት ሙያቸውን ለማሻሻል ጥረት የተደረገ ሲሆን፣ መመሪያውንና የአፈፃፀም ስልት ረቂቁን ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትም ለመፈፀም ተችሏል፡፡

- በኢትዮጵያ የሕዝብ የክብር መዝገብና የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን በተመለከተ ቀጣይ ተግባራት በመሠራት ላይ ሲሆኑ፣ ከነዚህም ውስጥ " የሕዝብ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን በማቋቋም የባለቤቶችና ዋነኛ ተባባሪ ድርጅቶች ዋናዋና የተግባር ዘርፎች" በሚል የተዘጋጀው ሁለተኛው ረቂቅ ለአስተያየት ቀርቧል፡፡

- በሀገሪቱ የቫይታል ስታቲስቲክስ ምዝገባና የስታቲስቲክስ ሥርዓትን ለመፍጠር የተዘጋጁ ዶክመንቶችን ወደፊት በሥራው ላይ የሚሣተፉ አስፈፃሚ ተቋማትን

ለማስተዋወቅ የሚያስችል መድረክ ከአዲስ አበባ ሥነ-ሕዝብ ጽ/ቤት ጋር በማዘጋጀት ጥናታዊ ጽሑፍ እና ተግታፊዎች ሊያውቋቸው የሚገቡ (Display) የሚደረጉ ዝግጅቶች ቀርበዋል።

## 2.5 የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናትን በተመለከተ

በ1993 ዓ.ም የባለሥልጣን መ/ቤቱን የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ርና የዓለም የሥራ ድርጅት (ILO) የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናት (Stand Alone Child Labour Survey) እንዲያካሂድ በጠየቁት መሠረት የጥናቱ የመስክ የመረጃ መሰብሰብ ሥራ መከናወኑ ይታወቃል። ይህንን ጥናት አስመልክቶ በበጀት ዓመቱ ከተከናወኑ ሥራዎች ውስጥ፡-

- የመረጃ ኤዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም መረጃውን ወደ ኮምፒውተር ማስገባት ሥራ ተጠናቋል፤ እንዲሁም መረጃ የማጽዳት (Cleaning) እና መረጃውን በኮምፒውተር ለማጠናቀር የፕሮግራም ዝግጅትና የፕሮሰሲንግ ሥራ ተከናውኗል፡

- ለጥናቱ በተዘጋጀው ማባዣ (raising factor) በመጠቀም የሕዝብ ብዛት የሚያሳዩ ውንጠረዦች የወጡ ሲሆን፤ ይህንኑ መረጃ ከሌሎች የጥናት ውጤቶች ጋር ለማነፃፀር ተሞክሯል፡

- የጥናቱንም ውጤት ለመተንተን የተለያዩ ሀገሮችን ልምድ ለማግኘት ከአዲስ አበባ የILO መ/ቤት ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን፤ የባለሙያ ድጋፍ በድርጅቱ በኩል እንዲቀርብ በተጠየቀው መሠረት አንድ ኤክስፐርት ከጀኔቫ እንዲመጣ ተደርጎ ከባለሥልጣኑ መ/ቤትና ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር በመሆን በጥናቱ ሪፖርት ይዘትና ቅርጽ ላይ ሰፋ ያለ ቴክኒካዊ ሥራዎች ተከናውነዋል።

- ለጥናቱ ሪፖርት ዝግጅት የተዘጋጁ በርካታ ውንጠረዦች ተተንትነና በአምስት ምዕራፍ ተከፍሎ የተዘጋጀ ረቂቅ የትንተና ሪፖርት ለመ/ቤቱ የፖሊሲ አማካሪ ኮሚቴ የቀረበ ሲሆን፤ ሪፖርቱን ኮሚቴው አይቶት አስፈላጊውን ማሻሻል በማድረግ የሪፖርት ዝግጅቱ ተጠናቋል። ይህም ሪፖርት ከ400 ገጽ በላይ የሆነ የስታቲስቲካዊ ውንጠረዦችንም የያዘ ነው።

2.6 **ማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ**

ሀ/ **የጤና ስታቲስቲክስ**

በየዓመቱ ከሁለተኛ የመረጃ ምንጭ (Data from Secondary Sources) የሚሰበሰቡ ጤና ነክ መረጃዎችን ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከክልል የጤና ቢሮዎች በመሰብሰብ የባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚያዘጋጀው ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል። በበጀት ዓመቱም ለ1993 ዓመታዊ ስታቲስቲክ መጽሔት ዝግጅት የሚሆኑ ጤና ነክ መረጃዎች ከኦሮሚያ ክልል በስተቀር ከሌሎች ክልሎች ተሰብስቦ በዓመታዊ መጽሔት እንዲካተት ተደርጓል።

ለ/ **የትምህርት ስታቲስቲክስ**

የ1993 ዓ.ም የትምህርት መረጃዎች ከትምህርት ሚኒስቴር ሙሉ በሙሉ የተገኘ ሲሆን፣ ለተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ ተዘጋጅተው በዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ላይ እንዲወጣ ተደርጓል።

ሐ/ **የባህልና ስፖርት ስታቲስቲክስ**

የ1993 ስፖርትና ባህል መረጃዎች ከፌደራል ስፖርት ኮሚሽንና ከባህል ሚኒስቴር ተጠይቆ የደረሰ ሲሆን፣ ለተጠቃሚዎች በሚሆን መልኩ ተዘጋጅተው በዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ላይ እንዲወጣ ተደረጓል።

መ/ **የሕግና ፍትህ ስታቲስቲክስ**

የ1993 የማረሚያ ቤቶችንና የፌደራል ፖሊስ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሆኑ መጠይቆች ለሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል መ/ቤቶች የተበተኑ ሲሆን፣ ከተበተኑ ቅጾች የተሰበሰቡት መረጃዎች በሚገባ ተጠናቅሮና ለተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ ተዘጋጅተው በዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ላይ እንዲወጣ ተደርጓል። ከሁለተኛ የመረጃ ምንጭ የሚገኙ መረጃዎችን ይዘት ለማሻሻል መረጃ ሰጪ ከሆኑ መ/ቤቶች ማለትም ከጡረታና ማሕበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን፣ ከፍትህ ሚ/ር፣ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከማኅበራት ማደራጃ ጽ/ቤት ከሚገኙ ባለሙያዎች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር

እየተሞከረ ነው። እንዲሁም ለሌሎች መንግሥታዊ መ/ቤቶች ከሚደረገው ዕገዛ ወጣቱን በሚመለከት ለሚዘጋጀው የፖሊሲ ፍሬም ወርክ በተቋቋመ ግብረ-ሃይል መ/ቤቱ በመሣተፍ ላይ ይገኛል።

## 2.7 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

ከኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በኩል የተዘጋጀው የአድማጭና ተመልካች አስተያየት መሰብሰቢያ ቅጾችን በመገምገም ሙያዊ አስተያየት በመ/ቤቱ ባለሙያዎች ተሰጥቷል።

# 3. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ

በ1994 በጀት ዓመት በብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራምና በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ አማካይነት የተከናወኑ የተለያዩ ጥናቶች በዘርፉ ተጠንተውና ሪፖርት ተዘጋጅቶላቸው ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ በዕቅድ የተያዙ ሲሆን፣ በዚሁም መሠረት ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ አፈፃፀሙ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 3.1 የተፈጥሮ ሀብትና የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

### 3.1.1 ዓመታዊ የግብርና ናሙና ጥናት

#### ሀ. የሰብል ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

- በ1994 ዓ.ም ከመስከረም ጀምሮ ለተካሄደው የሰብል ትንበያ ጥናት መረጃ ቅንብር የሚያገለግል የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

- የ1994 ዓ.ም የሰብል ትንበያ ጥናት መረጃ ተቀነባብሮ፣ የሪፖርት ዝግጅቱ ተጠናቆና ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

#### ለ. የእርሻ መሬት ስፋት መረጃን በተመለከተ

- 1993 የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1993 ዓ.ም በበልግ ወቅት የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት መረጃ በመስክ የመሰብሰቡ ተግባር ተጠናቆ የኢዲቲንግ ኮዲንግና የቬሪፊኬሽን ሥራ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ እንዲሁም የሪፖርቱ ዝግጅቱ አልቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች በመሰራጨት ላይ ይገኛል።

- የ1994 ዓ.ም የዋናው መኸር ወቅት የሰብል ምርት መጠንና የታረሰ መሬት ስፋት መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ የኢዲቲንግ፣ ኮዲንግና የቬሪፊኬሽን ሥራ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ከ60 በመቶ በላይ የሚሆነው መረጃ ወደ ኮምፒውተር ገብቶና ተቀነባብሮ የሦስት ክልሎች መረጃ በባለሙያዎች በመገምገም ላይ ይገኛል። የቀሪዎቹ ክልሎች መረጃ ደግሞ በመቀነባበር ላይ ነው።

ሐ. <u>የእርሻ ሥራ አመራር ሁኔታን /Farm Management Practices/ በተመለከተ</u>

- የ1993 ዓ.ም የዋናው መኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ ሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

- የ1993 ዓ.ም የበልግ የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ የማቀነባበሩ ተግባር ተጠናቆ ሪፖርቱ ለሕትመት ተልኳል።

- የ1994 ዓ.ም የዋናው መኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ የኢዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ከ60 በመቶ በላይ የሚሆነው መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባትና የማፅዳት ሥራ ተከናውኗል። በተጨማሪም የሦስት ክልሎች መረጃ ተቀነባብሮ በባለሙያዎች በመገምገም ላይ ሲሆን፣ የቀሪዎቹ ክልሎች መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

መ. <u>መሬት አጠቃቀምን / Land Utilization/ በተመለከተ</u>

የ1994 የመሬት አጠቃቀም መረጃ የመሰብሰቡ ተግባር ተጠናቆ የቅንብር ሥራው በመከናወን ላይ ሲሆን፣ መረጃው ከእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ

መረጃ ጋር በተጓዳኝ የሚሠራ በመሆኑ የሦስት ክልሎች መረጃ ተቀነባብሮ በባለሙያዎች በመገምገም ላይ ይገኛል።

ሠ. <u>የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች መረጃን በተመለከተ</u>

- በ1993 ዓ.ም በየካቲት ወር በተካሄደው የቤት እንስሳት ጥናት የተሰበሰበው መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም የመረጃ ቅንብሩ ሥራ ተጠናቋል። የመረጃው አስተማማኝነት ግምገማ ከተከናወነ በኋላ የሪፖርት ዝግጅቱ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።
- የ1994 ዓ.ም የግብርና ቆጠራ የቤት እንስሳት መረጃው ከመስከ ተሰብስቦ የኤዲቲንግ ፣ ኮዲንግና የቬሪፊኬሽን ሥራ በመከናወን ላይ ሲሆን፤ የአንድ ክልል/ ቤንሻንጉል ጉሙዝ/ መረጃ ወደ ኮምፒውተር ገብቶ መረጃውን የማፅዳት ሥራ ተጠናቋል። የዚሁ ክልል ውጤትም በባለሙያዎች በመገምገም ላይ ይገኛል።

2 <u>የ1994 የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራን በተመለከተ ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት</u>

የግብርና ናሙና ቆጠራ በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በመካሄድ ላይ ያለ ሲሆን፤ በመንግስት በኩል ከፍተኛ በጀት ተመድቦለት በመላ አገሪቱ በ464 ወረዳዎች ውስጥ በገጠር በናሙና በተመረጡ 11,199 እና በከተማ 4,100 በአጠቃላይ 15,299 የቆጠራ ቦታዎች 17,434 የሰው ኃይል በማሰማራት ከመስከረም 2 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ በገጠር የአርሶ አደሩ አካባቢ፣ በከተማ፣ በሰፋፊ /መካከለኛ የግል ንግድ፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች (Institutional Farms) በመስከ መረጃ የመሰብሰብ ሥራ ተጠናቋል። ከእነዚሁም የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ።

<u>የግብርና ናሙና ቆጠራ ዝግጅትን በተመለከተ</u>

- የግብርና ናሙና ቆጠራ ቅድመ ዝግጅት ሥራዎች የሚያከናውኑ ሰባት የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተቋቁመው፤ በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የመጠይቆች፣ የመመሪያና የሌሎች አሠራር መመሪያዎችን ዝግጅት ሥራ በማከናወን በየወቅቱ ለግብርና ናሙና ቆጠራው እንዲውሉ ከማድረጉም በላይ

ስለኮሚቴዎቹ ሥራ በየወቅቱ ለግብርና ቆጠራ ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት አቅርበዋል።

- ለግብርና ናሙና ቆጠራ የሚያገለግል የስፋትና የምርት የአካባቢ መለኪያ ኮድ ቡኮች ዝግጅት ተጠናቆና ታትሞ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

- በግብርና ናሙና ቆጠራ የሚሳተፉ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል። በተጨማሪም በመስክ ለመረጃ መሰብሰቡ ተግባር የሚውሉ የቆጠራ ዶክመንቶችና (መጠይቆችና መመሪያዎች) የመስክ ቁሳቁስ ሥርጭት ዝርዝር በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ኮሚቴዎች ቀርቧል። በዝርዝሩ መሠረት የቆጠራ ዶክመንቶችና የመስክ ቁሳቁሶች በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ደርሶ አስፈላጊው መረጃ ከመስክ ተሰብስቧል።

- በግብርና ናሙና ቆጠራ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ከመስጠቱም በላይ፣ በሰብል ትንበያ መረጃ መሰብሰብ ወቅት ከሁሉም የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ስለቆጠራው አፈፃፀም ተነስተው ለነበሩ የቴክኒክና ተዛማጅ ጥያቄዎች ከዋናው መ/ቤት ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል።

- ለነባር ስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ስለግብርና ናሙና ቆጠራው አጠቃላይ ይዘትና የቴክኒክ አሠራሩን በተመለከተ የአራት ቀናት ሥልጠና በዋናው መ/ቤት እንዲሰጣቸው ተደርጓል።

<u>የግብርና ናሙና ቆጠራ የመረጃ መሰብሰብና የቅንብር ሥራን በተመለከተ</u>

- የ1994 ግብርና ናሙና ቆጠራ አካል የሆነው በግብርና የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ወይም ባለይዞታዎች ዲሞግራፊያዊ ባሕሪያት መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ ኢዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም የመረጃ ማቀነባበር ሥራ ተጠናቋል።

- በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለሚካሄደው የቤት እንስሳት ቆጠራ ዝግጅቱ ለአፋርና ሶማሌ ክልል በተናጠል የቆጠራ ዘዴና ቆጠራው የሚካሄድበት ወቅት የሚገልጽ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቷል።

- በየካቲት ወር 1994 ዓ.ም የከተማ አካባቢ ግብርና ናሙና ቆጠራና በመጋቢት ወር 1994 ዓ.ም የእርሻ መሣሪያዎችና በሌሎች የግብርና ነክ ጥያቄዎች ዙሪያ

የሚሰበሰበው መረጃ ከመስከ ተሰብስቦ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ መረጃ የተሰበሰበባቸው መጠይቆች ወደዋናው መ/ቤት ገቢ ተደርገዋል።

- የግብርና ናሙና ቆጠራው አካል የሆነው የሰፋፊና መካከለኛ የግል ንግድ፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎችን መረጃ የመሰብሰብ ተግባር ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ዶክመንቱ ወደዋናው መ/ቤት ገቢ ተደርጓል።

- በ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ኢዲትና ኮድ ለማድረግ እንዲሁም ለኮምፒውተር ዳታ ኢንትሪና ዳታ ክሊኒንግ ሥራ የኮምፒውተር ኢዲት ስፔስፊኬሽን ማንዋል ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም የሥንጠረዥ ፕላን ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ውሏል።

- የኩራዝ ወረዳ የአርብቶ አደር አካባቢ በመሆኑ የአርብቶ አደሩን የቆጠራ መጠይቅና የቆጠራ ዘዴ በመጠቀም ለብቻው ቆጠራ እንዲደረግለት በተወሰነው መሠረት የቤት እንስሳት ቆጠራ ተግባር በሚያዚያ ወር 1994 ዓ.ም ተካሂዶ፣ መረጃ የተሰበሰበባቸው መጠይቆች ወደዋናው መ/ቤት እንዲመጡ ተደርጓል።

- ከ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ ለሚገኙ የተለያዩ ግብርና ነክ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ለሚወጡ ስታቲስቲካል ሪፖርቶች የሚሆኑ የሪፖርት ዝግጅት /የጽሑፍ ሥራ/ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

### 3.1.3 <u>ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች</u>

በUNSD ለቀረቡ የአካባቢያዊ ስታቲስቲክስን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ከሌሎች መ/ቤቶች በማሰባሰብ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተልኳል።

## 3.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት

### 3.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክሶችን ሥራ በተመለከተ

#### ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራች ዋጋ ጥናት

- ከሚያዚያ 1993 እስከ ሰኔ 1993 ዓ.ም ድረስ ያሉት መረጃዎች የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ ለሕትመት ተዘጋጅተዋል::

- ከመስከረም ወር 1994 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ ወር 1994 ዓ.ም ያሉት መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበው የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቆና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለሕትመት ተልኳል::

- ለ1995 በጀት ዓመት የሚያገለግሉ መጠይቆች ተዘጋጅተው በሕትመት ላይ ይገኛሉ::

#### ለ. በገጠር የችርቻሮ ዋጋ ጥናት

- የሚያዚያ 1993 እስከ ሰኔ 1993 ድረስ ያለው መረጃ የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል::

- የገጠር የችርቻሮ ዋጋ ጥናት መረጃ ሲሰበሰብ የነበረው የገበያ ቦታዎችን ስርጭት በተከተለ መልኩ ሳይሆን ለግብርና ናሙና ጥናት በሚመረጡ የቆጠራ ቦታዎች ነዋሪ የሆኑ ቤተሰቦች የሚገበያዩባቸው ገበያዎች ላይ ያተኮረ እንደነበረ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ የገጠሩ የችርቻሮ ዋጋ ጥናት መረጃ አገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ስርዓት አንፃር ሲገመገም ጠቀሜታው የጎላ አልሆነም:: በመሆኑም የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስን ለማስላት የተመረጡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች (Basket of Commodities) በእነዚህ የገጠር ገበያዎች በአብዛኛው አለመገኘት ሳቢያ የገጠር ችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከሐምሌ 1993 ጀምሮ እንዲቋረጥ በማድረግ፣ ከየዞኑ የደራ የገበያ ቦታዎችን በመምረጥ የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በገበያ ደረጃ ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጓል::

ሐ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

- <u>በ45 ከተሞች የሚካሄደው ነባር የችርቻሮ ዋጋ ጥናትን በተመለከተ</u>

  ከሚያዝያ ወር 1993 እስከ ሰኔ 1993 ዓ.ም ደረስ ያለው የዋጋ መረጃ ሪፖርት ተጠናቆ ለሕትመት ተልኳል።

- <u>በ106 ከተሞች የሚካሄደው አዲስ የችርቻሮ ዋጋ ጥናትን በተመለከተ</u>

- በ106 ከተሞች ውስጥ በሚገኙ 119 የገበያ ቦታዎች የሚካሄደው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከሐምሌ ወር 1993 እስከ መጋቢት ወር 1994 ዓ.ም ያሉት መረጃዎች ተሰብስበው የዳታ ክሊኒንግ ሥራ ተጠናቋል።

- የሚያዝያ ወር 1994 ዓ.ም መረጃ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመከናወን ላይ ነው።
- የግንቦትና የሰኔ ወር 1994 ዓ.ም መረጃ በመቀነባበር ላይ ይገኛል።

መ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ</u>

- <u>የ 1988 ዓ.ም መሠረት ያደረጉ (ነባር) የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች</u>

  ከዚህ ቀደም ሲሠሩ የነበሩ የአገር አቀፍ፣ የገጠርና የከተማ የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶችን በተመለከተ እስከ ሰኔ ወር 1993 ዓ.ም. ያሉት ወርሃዊ ኢንዴክሶች ተዘጋጅተውና ታትመው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል።

- <u>የአዲስ አበባ ከተማ ኢንዴክስ</u>

  የአዲስ አበባ ከተማ ኢንዴክስ እስከ ግንቦት ወር 1994 ዓ.ም ያሉት መረጃዎች ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ ሲሆን፣ የሰኔ ወር መረጃ ተቀነባብሮ ለሕትመት ተልኳል። የነባሩ ኢንዴክስ ስራ እስከ ነሐሴ ወር 1994 ዓ.ም ድረስ ቀጥሎ ከዚያ በኋላ በአዲሱ ኢንዴክስ ይተካል።

- <u>የ1993 ዓ.ም መሠረት የሚያደርገው የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ</u>

  አዲሱን የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት እንዲቻል በቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ወቅት የተገኘውን የወጪ መጠን የመቶኛ ድርሻ (weight) በመውሰድ የታህሣሥን ወር 1993 ዓ.ም መሠረት አድርጎ የተሰላው የ11 ክልሎችና የአገር አቀፍ ኢንዴክስ ከጥር እስከ መጋቢት 1994 ዓ.ም ድረስ ያለው ኢንዴክስ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ የሚያዝያና የግንቦት ወር 1994 ዓ.ም መረጃ በመቀነባበር ላይ ይገኛል፡፡

## ሠ. <u>ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት</u>

በ1991/92 ዓ.ም የተካሄደው የቤተሰብ ገቢ ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ እንዲሁም ለ1992 ዓ.ምን መሠረት ያደረገው የአገር አቀፍና የክልሎች የሸማች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አኃዞችን በተመለከተ ከተለያዩ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የተወከሉ ባለሙያዎችና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ለመጡ ከ90 በላይ ተሣታፊዎች የሁለት ቀን የሪፓርት ማስተዋወቂያና ሥርጭት ሴሚናር ተካሂዷል፡፡

## 3.3 <u>የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

### 3.3.1 <u>የኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና ኮንስትራክሽን ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

#### ሀ. <u>የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ጥናት</u>

- የ1992 ዓ.ም በተመለከተ የዘርፉ ጥናት የመረጃ መሰብሰብ፣ የኤዲቲንግና ኮዲንግ፣ እንዲሁም የሠንጠረዥ ቅንብር ሥራ ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

- የ1993 የዘርፉ የመረጃ መሰብሰብ፣ ኤዲቲንግና ኮዲንግ እንዲሁም መረጃውን ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ ተጠናቆ የሠንጠረዥ ማውጣት ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

- በ1995 በጀት ዓመት ሊካሄዱ ለታቀዱት የጎጆ/ዕደ ጥበብ ኢንዱስትሪዎች የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ፣ ለመደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ

እና አከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት የሥራ ክንውኗ የጊዜ ሰሌዳና የበጀት ግምት ተዘጋጅቶ ቀርቧል። ለጥናቶች የሚውሉ መጠይቆች የከለሳ ሥራም በመከናወን ላይ ይገኛል።

ለ. <u>የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መረጃን በሚመለከት፣</u>

- የ1992 የዘርፉ መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ በዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መጽሔት ውስጥ ተካትቶ እንዲወጣ ተደርጎ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።
- የኤሌክትሪ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የ1993 ዓ.ም ጥናት መረጃ ከመስክ ተሰብስቧል።

ሐ. <u>የውጭ የንግድ፣ የትራንስፖርት፣ መገናኛና ፋይናንስ መረጃ፣</u>

- እ.አ.አ የ2000ን መረጃ የያዘው የውጪ ንግድ መጽሔት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- እ.አ.አ የ2001 የውጭ ንግድ መረጃ እስከ ሴብተምበር 2001 ድረስ ያለው መረጃ ተሰብስቦ የመረጃ ቅንብርና የእርማት ሥራው በመሠራት ላይ ይገኛል።

መ. <u>የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ኢንደክስ ሥራ</u>

- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የ1992 ዓ.ም መረጃን የሚያካትተው የኢንደክስ ሥራ የመረጃ ቅንብር ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1993ን ዓ.ም መረጃ የሚያካትተው የኢንደክስ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

ዥ 1 **በ1994 በጀት ዓመት የጥናቶች የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም** (በመቶኛ)

| የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1993 በጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወነ | የ1994 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| **የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ** | | | | | |
| የግብርና ሰብል ትንበያ ጥናት | አዲስ | 15 | 85 | 85 | 100 |
| የዋናው መኸር ወቅት የግብርና ናሙና ቆጠራ | አዲስ | 15 | 75 | 65 | 86 |
| የበልግ ወቅት ጥናት | አዲስ | - | 65 | 65 | 100 |
| በገጠር በአርሶአደሩ አካባቢ የቤት እንስሳት ናሙና ቆጠራ | አዲስ | - | 65 | 65 | 100 |
| በከተሞች አካባቢ የግብርና ናሙና ቆጠራ | አዲስ | - | 75 | 69 | 92 |
| የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ግብርና ናሙና ቆጠራ | አዲስ | - | 69 | 65 | 94 |
| ሌሎች ግብርና ነክ መረጃዎች (የእርሻ መሣሪያዎች፣ የኤክስቴንሽን መረሃ-ግብር ዙሪያ...ወዘተ) | - | - | 65 | 65 | 100 |
| **የዋጋዎች ጥናት** | | | | | |
| የ1993 የአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር | ነባር | 95 | 5 | 5 | 100 |
| የ1994 የአምራቾች ዋጋ ጥናት በገጠር | አዲስ | 15 | 85 | 85 | 100 |
| የ1994 የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተማ | አዲስ | 15 | 85 | 85 | 100 |
| የ1992 የትላል. የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | ነባር | 87.6 | 12.4 | 12.4 | 100 |
| የ1993 የትላል. የመካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ. ጥናት | አዲስ | - | 95 | 77 | 81 |
| **ዋጋዎች ኢንዴክስ ሥራ** | | | | | |
| የአዲስ አበባ የዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | - | 100 | 100 | 100 |
| የአገር አቀፍ የዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | - | 90 | 81 | 90 |

4. **የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትና የካርቶግራፊ ሥራ**

በየዓመቱ በባለሥልጣኑ መ/ቤት ለሚካሄዱ የተለያዩ የስታቲስቲክስ ጥናቶች የሚያገለግሉ የአሠራር ዘዴዎችና (Methodologies) የአፈፃፀም መመሪያዎችን እንደዚሁም ለጥናቶች የሚያገለግሉ መጠይቆችና ቅጾች ጥራት፣ ብቃትና ወካይነታቸውን በማረጋገጥ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በበጀት ዓመቱ በክፍሉ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውናል፡፡

## 4.1 የሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅት

- የ1993 ዓ.ም የልጆች ሥራ ስምሪት ጥናትን አስመልክቶ የማባዣ ቁጥሮች (Raising facror) ተሰርቶና ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል፡፡
- ለግብርና ናሙና ቆጠራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ዶክመንቶችንና ለCrop forecast የሚያስፈልገውን የማባዣ ቁጥሮች (raising factor) ዝግጅት ተሰርቷል፡፡
- በመካሄድ ላይ ላለው አገር አቀፍ የግብርና ናሙና ቆጠራ የማባዣ ቁጥሮች (raising factor) ዝግጅት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡
- የሰፋፊ/መካከለኛ የግል ንግድ፣ የመንግሥትና የድርጅት ማህበራት እርሻዎችን ዝርዝር update ለማድረግ ከዚህ ቀደም የተሰበሰበውን መረጃ በዞንና በወረዳ ደረጃ እንዲዘጋጅ ወደ ቅ/ጽ/ቤቶች ተልኮ መረጃው ተሞልቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡
- የግብርና ናሙና ቆጠራ አካል የሆነው የከተማ ግብርና ቆጠራን በተመለከተ መረጃውን በወረዳ ደረጃ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያስችል ዲዛይን ተዘጋጅቶ የመስክ ፍተሻ እንዲካሄድ ተደርጓል፡፡
- ለኤዲቲንግና ኮዲንግ የሚያገለግሉ የአካባቢ መለያ ኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## 4.2 ካርቶግራፊ፣ መዛግብት አያያዝና ስታንደርድስን በተመለከተ

- ለግብርና ቆጠራው የሚያስፈልጉ የተለያዩ የቆጠራ ቦታና የወረዳ ካርታዎችን ለይቶ በማውጣት አሳትሞ ለሚመለከተው ክፍል በመስጠት በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡
- ከሶማሌና አፋር ክልሎች ውጪ የሚገኙ የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች ላይ ለሚካሄደው ቆጠራ የክፍሉ ባለሙያዎች የመስክ ጉብኝት በማድረግ ቆጠራው ስለሚካሄድበት ዘዴና ጊዜ አጥንተው ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርቱን አቅርቧል፡፡

- መረጃ የሚሰበሰብባቸው የምርት ዕቃዎችና ሌሎችን የመፈረጅ ሥራ ጥናትን በተመለከተ ውይይት እየተካሄደ ይገኛል፡፡

- በመ/ቤቱ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መምሪያዎች የሚያዘጋጁቸው ሪፖርቶች ደረጃቸውን የጠበቁ የሚሆኑበት መንገድ ውይይት እየተካሄደ ነው፡፡

## 5. የ1993 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅትን በተመለከተ

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በየዓመቱ እያዘጋጀ የሚያወጣውንና የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ-ነክ ሁኔታዎችን የሚገልጹ መረጃዎች ለሚይዘው የ1993 ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚሆን መረጃ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተሰብስቦ፣ ለመረጃ ተጠቃሚዎች በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቶና ታትሞ ተሰራጭቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ የ1993 ዓ.ም ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔቱ ውስጥ የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲካተቱ የተደረገ ሲሆን እነዚህም፡-

- የሥነ ሕዝብ መረጃዎች፣
- የግብርና መረጃዎች፣
- የማዕድንና ምርት መረጃዎች፣
- የማምረቻና የኤሌክትሪክ ኢነርጂ መረጃዎች፣
- የሕንፃ ሥራ መረጃዎች፣
- የትራንስፓርትና መገናኛ መረጃዎች፣
- የውጭ አገር ንግድ መረጃዎች፣
- ዓመታዊ የሀገር ሃብት መረጃዎች
- የመንግሥት ገንዘብ /Public Finance/ መረጃዎች፣
- የባንክ ሥራዎችና የአከፋፈል ሚዛን መረጃዎች፣
- የመድህን /ኢንሹራንስ/መረጃዎች፣
- የዕቃዎች ዋጋ መረጃዎች፣
- የጤናና የትምህርት መረጃዎች፣
- የሕግና ደንብ መረጃዎች፣
- የስፖርትና ሲኒማ መረጃዎች፣...ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 6 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- ከተለያዩ ድርጅቶችና ተቋማት እንዲሁም ግለሰብ መረጃ ተጠቃሚዎች የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች በመቀበል አስፈላጊውን ስታቲስቲካዊ መረጃና ቴክኒካዊ ድጋፍ አድርጓል።
- በ1994 ዓ.ም በመካሄድ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በተለያዩ ኮሚቴዎች በአባልነት፣ በቆጠራው ለሚሰጥ መረጃ ሰብሳቢዎችና ተቆጣጣሪዎች በአሠልጣኝነት እንዲሁም በመስከረም ወር በተካሄደው የሰብል ትንበያ ጥናት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ላይ በመስክ ሥራ ቁጥጥርና ግምገማ ተሳታፊ ሆነዋል።
- ለመ/ቤቱ ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚውሉና ከሌሎች መ/ቤቶች መሰብሰብ ያለባቸው መረጃዎች በአብዛኛው እንዲሰበሰቡ የተደረገ ሲሆን፣ ለተጠቃሚዎች በሚሆን መልኩ ተዘጋጅተው በመጽሔቱ ላይ እንዲወጡ ተደርጓል።
- ከጥቅምት ወር 1994 ዓ.ም ጀምሮ በቆጠራው ከመስክ ተሰብስበው በመጡ መረጃዎች ላይ በመከናወን ላይ ለሚገኘው ኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና ቬሪፊኬሽን ሥራ የመ/ቤቱ ባለሙያዎች በተቆጣጣሪነትና ለአስተባባሪነት ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

## 7. በማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት

- ለኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የተዘጋጁ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎች ማለትም በራሪ ጽሑፎች፣ ፖስተሮች፣ መፈክሮች፣ መዝሙርና የቪዲዮ ክር ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ለመገናኛ ብዙሃን (ለኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት) እንዲደርስ በማድረግ ለቅስቀሳ ተግባር እንዲውሉ ተደርጓል፣
- ለግብርና ናሙና ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ከተመረጡት ድራማዎች "ናሙና" የተሰኘው ድራማ ለቴሌቪዥንና ለሬዲዮ ስርጭት በሚያመች መልኩ እንዲዘጋጅ ተደርጎ ለሕዝብ ቀርቧል።

- ስለግብርና ናሙና ቆጠራው ዓላማ፣ ይዘት፣ አጀማመር... ወዘተ በተመለከተ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊዎች መግለጫዎችን በሬዲዮና በቴሌቪዥን እንዲሁም በጋዜጣ ታትመው እንዲወጡ አስፈላጊው ድጋፍ የተሰጠ ሲሆን፣ በተለይም ደግሞ በከተሞች አካባቢ እርሻዎች፣ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊካሄድ ስለታሰበው የቤት እንስሳት ቆጠራና ስለሰፋፊና መካከለኛ የግል ንግድ፣ የመንግሥትና የድርጅት እርሻዎች በመ/ቤቱ ኃላፊዎች መግለጫዎች እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም መ/ቤቱ ላካሄዳቸው ጥናቶች የ1994 ዓ.ም የመኸርን ወቅት ምርት በተመለከተ የተዘጋጀውን የፕሬስ ሪሊዝና በኢንዱስትሪ ዘርፍ በተደረጉ ጥናቶች የተገኙ ውጤቶችን ለመገናኛ ብዙሃን በመስጠት ዜናዎች እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡

- በኢፌዲሪ የማስታወቂያ ሚኒስቴር አማካይነት " የግብርና ቆጠራ ምንድን ነው?" በሚል ርዕስ ስለአጠቃላይ የግብርና ስታቲስቲክስና መረጃ አያያዝ እንዲሁም በመካሄድ ላይ ስላለው የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ ሂደት ግንዛቤ ለማስጨበጥ የግማሽ ቀን የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡ በዚህ ፓናል ውይይት ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በም/ዋና ሥራ አስኪያጅ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የብሔራዊ አካውንትስ መምሪያ፣ ከግብርና ሚኒስቴር የኤክስቴንሽን መምሪያና ከእንስሳት ገበያ ባለሥልጣን የፕላንና ፕሮጀክት መምሪያ ኃላፊዎች የግብርና ናሙና ቆጠራን አስፈላጊነትን በተመለከተ ጥናታዊ ጽሑፎች አዘጋጅተው ለውይይት አቅርበዋል፡፡

- ስለግብርና ናሙና ቆጠራ እንቅስቃሴ የአንዱን አካባቢ ለሌላው ማሣወቁ በሕብረተሰቡ ዘንድ የሚፈጥረውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ እንዲረዳ በማሰብ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮና ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኞች ጋር በመሆን የተደረጉትን የመስክ ሥራ ጉብኝት ሪፖርቶች በዜናዎችና በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች በተለያዩ ቋንቋዎች እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡

- በባለሥልጣኑ መ/ቤት የተዘጋጁ 5,959 (አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ዘጠኝ) ሪፖርቶች ለ350 መ/ቤቶችና የመረጃው ተጠቃሚዎች በነፃ እንዲሰራጩ የተደረገ ሲሆን፣ 3,332 (ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሣ ሁለት) ሪፖርቶች ደግሞ በብር 85,669.85 (ሰማንያ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሣ ዘጠኝ ብር ከሰማንያ ሣንቲም/ ሽያጭ ተፈፅሟል፡፡ በበጀት ዓመቱ በጠቅላላው 9,291(ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አንድ) ሪፖርቶች ስርጭት ተካሂዷል፡፡

- በበጀት ዓመቱ የመ/ቤቱን አጠቃላይ መግለጫ የያዘ ብሮሸርና የቀን መቁጠሪያዎች ተዘጋጅተውና ታትመው ለሚመለከታቸው ተሰራጭተዋል::

- የመ/ቤቱ ቤተ መፃሕፍት ከውጭና ከመ/ቤቱ ለመጡ ተጠቃሚዎች አገልግሎት የሰጠ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ከውጭና ከአገር ውስጥ ለመጡና መረጃ ለሚፈልጉ እንግዶች አስፈላጊው መረጃ ተሰጥቷል:: እንዲሁም የመ/ቤቱን ቤተመጻሕፍት የብሪቲሽ ካውንስል ቤተመፃሕፍት አባል በማድረግ የመ/ቤቱን ሠራተኞች የተሻለ ግልጋሎት እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ የቤተመፃሕፍትና ዶክመንቴሽን አገልግሎት የተጠቃሚዎች ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶና ፀድቆ በሥራ ላይ ውሏል::

- አሁን ያለው የቤተመፃሕፍቱን አገልግሎት የበለጠ ለማዘመን እንዲቻልና የተጠቃሚዎችን የመጻሕፍትና መጽሔቶች የማንበብ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የተለያዩ ዓይነት መጽሔቶች የኮንትራት ውልና የአዳዲስ መፃሕፍት ግዢ ከመምሪያዎችና አገልግሎቶች በቀረበው ጥያቄ መሠረት ተፈጽሟል::

## 8. የሥራ አመራርና ሥልጠና አገልግሎት

- የመ/ቤቱ የሥራ ሽፋን በየጊዜው እያደገ በመምጣቱ ምክንያት ተጨማሪ የሰው ኃይል በቋሚነት እንዲቀጠር ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የቀረበው የ195 የሥራ መደብ ጥያቄ መፈቀዱ ይታወቃል:: ይህም የተፈቀደው የሰው ኃይል የሥራ ዝርዝር ተዘጋጅቶ ለኮሚሽኑ ተልኮና ምደባው ተሠርቶ የደረሰን ሲሆን፣ የተፈቀደውን የሰው ኃይል በቅጥርና በውስጥ ዕድገት የማሟላት ሂደት በሚቀጥለው በጀት ዓመት ይከናወናል::

- የመ/ቤቱ የሥራ ሽፋን በየጊዜው እየጨመረ ይገኛል:: በመሆኑም ለአንዳንድ መምሪያዎችና አገልግሎቶች የተፈቀደው የሰው ኃይል አሁን ከሚሰራው ሥራ አንፃር ሲታይ በቂ አይደለም:: ይህ ችግር ጎልቶ ከታየባቸው ውስጥ የሕግ አገልግሎት አንዱ ሲሆን፣ አገልግሎቱ ባለው የሰው ኃይል በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የሚነሱ የሕግ ጉዳዮችን ለመከታተል አስቸጋሪ ሆኗል:: ይህን ችግር ለመቅረፍ ተጨማሪ የሦስት ነገረፈጅ የሥራ መደብ እንዲፈቀድ ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጥያቄ ቀርቦ ምላሹ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

## 9. የሕግ አገልግሎት

- የመ/ቤቱ ባልደረቦች በነበሩበት ጊዜ የተሰጣቸውን የመንግሥት ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ በሚመለከታቸው ፍርድ ቤትና በመ/ቤቱ በተሰጣቸው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መሠረት በጠቅላላው በጉድለት ከሚታየው ብር 91,482.56 ውስጥ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ብር 74,055.29 ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል።

- የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች በተለያዩ ጊዜያት በሰዎች ላይ ላደረሱት ጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው በጠቅላላው ብር 404,840.20 በሚመለከተው ፍርድ ቤት በክሱ አቅርበው እየታየላቸው ይገኛል።

- እንደዚሁም በመ/ቤቱ ሠራተኞች የነበሩ መ/ቤቱ የሚፈልግባቸውን በጠቅላላው ብር 77,030.66 ገቢ እንዲያደርጉ ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት አቅርቦ ውሣኔ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

- በተጨማሪ በመደበኛና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ፍርድ ቤት ወደ ሥራ እንመለስ ጥያቄ ያቀረቡ ሠራተኞችን ጥያቄ ፍርድ ቤቶቹ ውድቅ አድርገው መ/ቤቱ በነፃ ተሰናብቷል።

## 10. የኦዲት አገልግሎት

- አገልግሎቱ የዋናው መ/ቤትንና የ47 ቱን ቅ/ጽ/ቤቶች የሚንቀሳቀሰውን በርካታ የገንዘብ ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት ሂሳቡን በቅድሚያ እየመረመረ አስፈላጊውን ማጣራት እያከናወነ ክፍያዎች እንዲፈፀሙ ያደርጋል። በዚሁ መሠረት በበጀት ዓመቱ 129,994,051 ብር ከዋናው መ/ቤትና ከ47ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ቀርቦ ቅድመ ምርመራ አድርጓል። እንደዚሁም የብር 86,165,542 ወጪዎችን ዝርዝር ምርመራ አካሂዶ ሂሳቡ እንዲወራረድ ተደርጓል፤

- በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው ፕሮጀክቶች ለየቅ/ጽ/ቤቶቹ ገንዘብ በባንክ በኩል ሲላክ እና የተለያዩ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች የገንዘብ ጥያቄ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ቅድመ ምርመራ ተደርጓል፤

- ለመ/ቤቱ አገልግሎት የሚሰጡ የመስክ ተሽከርካሪዎችን የነዳጅ አጠቃቀም በተመለከተ የነዳጅ ደረሰኝ ወጪ፣ በመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ መሞላቱንና ተሽከርካሪዎች በሊትር ምን ያህል ኪሎሜትር እንደተጓዙ ቁጥጥር ተደርጓል፣

- የመንግሥት ገንዘብ በግለሰቦች እጅ ገብቶ ባለመመለሱ ምክንያት ጉዳዩ በፍርድ ቤት ደረጃ ሲታይ በማስረጃነት ለሚጠየቅ የኦዲት ሪፖርት አስፈላጊውን የሒሣብ ምርመራ በማካሄድ ለጠየቀው ፍ/ቤት አፋጣኝ ምላሽ ተሰጥቷል፣

- በተጨማሪ የ13 ቅ/ጽ/ቤቶችን ርክክብ የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ፣ ገንዘብ ያዥንና ንብረት ክፍል ሠራተኛን ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት በጠቅላላው ለ16 ጊዜ በቅ/ጽ/ቤቶቹ ድንገተኛ የሒሣብ ምርመራ ተካሂዷል፡፡

11. <u>የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት</u>

- መ/ቤቱ በ1994 በጀት ዓመት ሊያካሂዳቸው በዕቅድ የተያዙ የሁለት ፕሮጀክቶች (የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይና የግብርና ናሙና ቆጠራ) በጀት ከሚመለከታቸው መምሪያዎችና አገልግሎት ጋር በመሆን በወርሃዊ የሥራ መርሃ ግብሩ መሠረት ወርሃዊ የገንዘብ ፍላጎት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተላልፏል፣

- የመ/ቤቱን ወርሃዊና የሩብ ዓመት የፕሮጀክቶች የፊዚካልና ፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለበላይ አካል ተላልፏል፣

- ለ1995-97 የመ/ቤቱን የኢንቨስትመንት ፕሮግራም ከባለሥልጣኑ የስታቲስቲክስ ጥናት ቅደም ተከተል በመነሳት የበጀት ፍላጎቱን ለሚመለከተው አካል እንዲተላለፍ ተደርጓል፣

- ለ1995 የመ/ቤቱን የስታቲስቲክስ የሥራ ዕቅድና ለማስፈፀሚያ የሚውል የካፒታል በጀት ፍላጎት ከሚመለከታቸው መምሪያዎች ጋር በመሆን አዘጋጅቶ ለበላይ አካል አቅርቧል፡፡

## 12. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና

### 12.1 የሰው ኃይልን በተመለከተ

በ1994 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,480 ቋሚና 1,665 የኮንትራት በጠቅላላው 3,145 ሠራተኞች ነበሩ ። ከነዚህ ቋሚ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ውስጥ 38 ሠራተኞች በራሳቸው ፈቃድና በተለያዩ ምክንያቶች ሥራቸውን ለቀዋል፣ 28 ሠራተኞች በሞት ተለይተዋል እንደዚሁም አምስት ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ ሲሆን፣ የ104 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር ተፈጽሟል። በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከነበሩት 1,665 የኮንትራት ሠራተኞች በተጨማሪ 13,371 ጆማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 882 ሱፐርቫይዘሮች፣ 278 የዳታ ኢንትሪና የኢዲቲንግ ሠራተኞች፣ ስምንት ጊዜያዊ የመስክ ሥራ አስተባባሪዎች፣ 255 የአስተዳደርና የሂሳብ ሠራተኞች እንደዚሁም 42 ሹፌሮችና፣ አንድ ጆማሪ ስታቲስቲሽያን በድምሩ 14,837 አዲስ የኮንትራት ሠራተኞች ተቀጥረዋል። እንደዚሁም 14,289 ሠራተኞች ደግሞ ከሥራ ተሰናብተዋል። በመሆኑም ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም በመ/ቤቱ ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት 3,726 ሲሆን፣ ከእነዚህ ሠራተኞች ውስጥ 1,513 ቋሚና 2,213 ደግሞ ኮንትራት ሠራተኞች ናቸው። በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ያለው የመ/ቤቱ ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት በሠንጠረዥ 2 ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 2 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የሰው ኃይል ሁኔታ

| ተራ ቁጥር | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,480 | 1,665 | 3,145 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 104 | 14,837 | 14,941 |
| 3 | በጡረታ የተገለሉ | (5) | - | (5) |
| 4 | ሥራ የለቀቁ | (38) | (14,289) | (14,327) |
| 5 | በሞት የተለዩ | (28) | - | (28) |
| ድምር | | 1,513 | 2,213 | 3,726 |

የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሙያ ወይም በሥራ መደብ ሲተነተን 122 ፕሮፌሽናል፣ 940 መለስተኛ ፕሮፌሽናል እና 451 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው። የእነዚህ ሠራተኞች ብዛት በፆታ ሲለዩ ደግሞ 1,149 ወንዶች /75.9 በመቶ/ ሲሆን 364 ሴቶች /24.1 በመቶ/ ናቸው።

## 12.2 የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ

መ/ቤቱ በየጊዜው ለሚያካሂዳቸው ነባርና አዳዲስ ጥናቶች ያለውን የውስጠን የሰው ኃይል ወቅታዊ የሆነ ሥልጠና በመስጠት ሙያቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በየበጀት ዓመቱ ለሚካሄዱ ጥናቶች የመረጃ አሰባሰብና የመጠይቅ አሞላል ለመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ይሰጣል፡፡ በመሆኑም በ1994 በጀት ዓመት የሰው ኃይል ሥልጠናን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል፡፡

ሀ. በአዲስ መልክ ለተጀመረው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ከመላው አገሪቱ ከተመረጡ 119 የገበያ ቦታዎች መረጃ ለሚሰበስቡ ሠልጣኞች ከሰኔ 20 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሳምንት ሥልጠና በዋናው መ/ቤት የተሰጣቸው ሲሆን፣ ሠልጣኞቹም ወደተመደቡበት የገበያ ቦታ ተሠማርተው ወርሃዊ መረጃ በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ፡፡

ለ. በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው የግብርና ናሙና ቆጠራ በአዲስ አበባ በሁለት ማሰልጠኛ ማዕከላት ከዋናው መ/ቤት፣ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ከሌሎች መ/ቤቶች ለተውጣጡ 542 ባለሙያዎች ከሰኔ 5 ቀን 1993 እስከ ሰኔ 29 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ የአሠልጣኞች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ በተመሣሣይ ሁኔታ ከሐምሌ 13 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 23 ቀን 1993 ዓ.ም በ47 የተመረጡ የሥልጠና ማዕከላት ለ13,100 የመረጃ ሰብሳቢዎችን ለ2,430 ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና በመስጠት፣ ነሐሴ 24 ቀን 1993 ዓ.ም በማዕከል በተዘጋጀ የመመዘኛ ፈተና ውጤት መሠረት ብቃት ያላቸው ተመርጠው የመስክ ሥራውን ግንቦት 30 ቀን 1994 ዓ.ም ፈጽመው እንዲሰናበቱ ተደርጓል፡፡

ሐ. የ1994 ዓ.ም የግብርና ናሙና ቆጠራ አካል የሆነው በከተማ አካባቢ እርሻዎች ግብርና ቆጠራ ላይ ለሚሣተፉ 4405 መረጃ ሰብሳቢዎችና ለ881 ተቆጣጣሪዎች ከየካቲት 16 ቀን 1994 ዓ.ም እስከ የካቲት 20 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ አስፈላጊው ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

መ. በ1993 ዓ.ም ለአንድ ዓመት በጋና ሀገር የማስተርስ ዲግሪ ትምህርት የተከታተሉ ሁለት ባለሙያዎች ትምህርታቸውን አጠናቀው ኅዳር 1994 የተመለሱ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በ1991 ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከገቡት አራት የመ/ቤቱ ባልደረቦች መካከል ሦስቱ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደሥራ ተሰማርተዋል፡፡ እንዲሁም ሌሎች በ1992 ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የገቡ ሦስት ባለሙያዎች ሁለት በስታቲስቲክስ አንድ በዲሞግራፊ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡

ሠ. በበጀት ዓመቱ የመ/ቤቱን ሠራተኞች በተለያዩ የሥራ ለማሻሻል ስልጠናዎች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ የሥራ ብቃታቸውን ለማሻሻል በነበረው ዕቅድ መሠረት 21 ሠራተኞች በቢሮ አያያዝ ለ5 ቀናት፣ 2 ሠራተኞች በሰው ኃይል አደረጃጀት፣ 5 ሠራተኞች በዘመናዊ የማኀደር አያያዝ፣ አንድ ሠራተኛ በአጠቃላይ ንብረት አያያዝ፣ አንድ ሠራተኛ በውስጥ ቁጥጥር፣ አንድ ሠራተኛ በጠቅላላ ጥገና አስተዳደር፣ ሁለት ሠራተኞች ለዕቃ ግዢና አስተዳደር እያንዳንዳቸው ለአሥራ ሁለት ቀናት እንዲሁም አንድ ሠራተኛ በፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ለአሥራ ዘጠኝ ቀናት በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት እንዲሰለጥኑ የተደረገ ሲሆን፣ አንድ ሠራተኛ ደግሞ የመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን በሚሰጠው የመካኒክነት ስልጠና ከኀዳር 24/1994 ዓ.ም ጀምሮ የሁለት ወር ሥልጠና ተከታትሎ ያጠናቀቀና ሌላ አንድ ሠራተኛ ደግሞ በሞተር ጥገና በዚሁ ድርጅት በመሰልጠን ላይ ይገኛል።

ረ. የተሰበሰቡ የግብርና ናሙና ቆጠራ መረጃዎች ወደ ኮምፒውተር ከመግባታቸው በፊት ለሚከናወን የኢዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ለተቀጠሩ 161 የኢዲቲንግና ኮዲንግ ሠራተኞች በአጠቃላይ የግብርና ናሙና ቆጠራ መጠይቆች ላይ የ5 ቀናት ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

ሰ. ለ1994 ግብርና ናሙና ቆጠራ ምክንያት አዲስ በተከፈቱና በነባር ቅ/ጽ/ቤቶች በኦዲተርነት ለተቀጠሩ ባለሙያዎች ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ሥራዎችን እንዲያውቁ ለማድረግ በዋናው መ/ቤት የአንድ ቀን ትምህርታዊ ገለፃ ተደርጎላቸው ወደሥራቸው ተመልሰዋል።

ሸ. በ1994 ዓ.ም ከመጋቢት አጋማሽ ጀምሮ ለተካሄደው የ1993 ዓ.ም የትላልቅና የመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ከ22ቱ ነባር ቅ/ጽ/ቤቶችና ከዋናው መ/ቤት ለተውጣጡ 160 ባለሙያዎች ስለ ጥናቱ አፈፃፀም የተሰጠው ስልጠና ከመጋቢት 9 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 18 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ተግባራዊ ሆኗል።

ቀ. በ1997 ዓ.ም ለሚካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኮምፒውተራይዝድ የካርታ ሥራ ለማስጀመር ፕሮግራመሮችን በቅድሚያ ማሰልጠን በማስፈለጉ ሁለት የመ/ቤቱ ባለሙያዎች ለሶስት ወራት ናይሮቢ (ኬንያ) ሥልጠና አግኝተው ተመልሰዋል።

13. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ለ1994 በጀት ዓመት ለአጠቃላይ የባለሥልጣኑ መ/ቤት የመደበኛና የካፒታል ወጪ ብር 147,850,200 ከመንግሥት የተፈቀደ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 12,485,500 ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 135,364,700 ተፈቅዷል:: ይህውም ከተፈቀደው በጀት ውስጥ 8.45% ለመደበኛ በጀት የተያዘ ሲሆን፣ 91.55% ደግሞ ለካፒታል በጀት የተመደበ ነው::

ሀ. <u>የመደበኛ በጀት አጠቃቀም</u>

የተፈቀደው በጀት በሚከተለው የወጪ አርዕስቶች የተከፋፈለ ነው:: ይኸውም፦

- ለደመወዝ ..................ብር 11,130,700.00
- ለውሎ አበል .............." 40,000.00
- ለሥራ ማስኬጃ ............." 1,314,800.00 የተያዘ ነው::

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሥራ ላይ የዋለው መጠን፦

- ለደመወዝ ክፍያ ከተፈቀደው 11,130,700 ብር ውስጥ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 10,826,622 ሲሆን፣ ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ከተፈቀደው ብር 10,826,622 (97.3%) ወጪ ተደርጓል::

- ለውሎ አበል ክፍያ ከተፈቀደው ብር 40,000 ውስጥ በበጀት ዓመቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 11,514 ሲሆን፣ ወጪ ከተደረገው ብር 11,514 (100%) ብር ጥቅም ላይ ውሏል:: ይህም ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 28.8 በመቶ ነው::

- ለሥራ ማስኬጃ ከተፈቀደው 1,314,800 ብር ውስጥ በበጀት ዓመቱ ተጠይቆ ገቢ የሆነው ብር 268,051 ሲሆን፣ ብር 808,258 በሥራ ላይ ውሏል::

በ1994 በጀት ዓመት የመደበኛ በጀት አጠቃቀም ላይ የታየው ልዩነት መ/ቤቱ በ1993 ዓ.ም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚፈለግበት ብር

1,046,745 የፊሰስ ዕዳ በአንድ ጊዜ ስለተቆረጠበትና ይህውም ገንዘብ ቀደም ብሎ ከታሣቢ ስለተሰራበት ነው።

ለ1994 በጀት ዓመት ማለትም ከሐምሌ 1 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ለመደበኛ በጀት በእጅ ገቢ የሆነው ብር 10,998,353 ሲሆን፣ ወጪ የሆነው ደግሞ ብር 11,646,394 ነው። አፈፃፀሙ በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃር 105.6% ሲሆን፣ ከዓመቱ ከዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ደግሞ 93.3 በመቶ ይሆናል።

## ለ. የካፒታል በጀት አጠቃቀም

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1994 ለሚያካሂዳቸው ሁለት ፕሮግራሞች ብር 135,364,700 የተፈቀደ ሲሆን፣ ይህም ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 3,383,900፣ ለግብርና ናሙና ቆጠራ ፕሮግራም ደግሞ ብር 131,980,800 የተፈቀደ ነው።

ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ለተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ከተፈቀደው ላይ ብር 3,340,300 ገቢ የተደረገ ሲሆን፣ ለግብርና ናሙና ቆጠራ ደግሞ ከተፈቀደው ብር 131,965,800 ገቢ ሆኗል። ለሁለቱ ፕሮግራሞች ከተፈቀደው በጀት ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ብር 133,440,103 ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። ይህም ለሁለቱ ፕሮግራሞች ከተፈቀደው በጀት ጋር ሲነፃር አፈፃፀሙ 98.6 ሲሆን፣ ለተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ከተፈቀደው 77.8 በመቶ እና ለግብርና ናሙና ቆጠራ ደግሞ 99.1 በመቶ ጥቅም ላይ ውሏል።

ከተፈቀደው የመደበኛና የካፒታል በጀት ከሐምሌ 1 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 146,440,773 ሲሆን፣ ብር 145,086,497 ደግሞ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። ወጪ የተደረገው በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃርም 99.1 በመቶ ሲሆን፣ አሃዛዊ መረጃውም በሚከተሉት ሠንጠረዦች ላይ ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 3/ሀ **የ1994 በጀት ዓመት የመደበኛ በጀት አጠቃቀም**

| በጀት አጠቃቀም | ለ1995 በጀት ዓመት የመንግሥት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | በበጀት ዓመት ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቶ በእጅ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት 03 እና 04 |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| ደመወዝ | 11,130,700 | 10,826,622 | 10,826,622 | - |
| ውሎ አበል | 40,000 | 40,000 | 11,514 | 28,486 |
| ሥራ ማስኬጃ | 1,314,800 | 268,051 | 808,258 | (540,207) |
| ድምር | 12,485,500 | 11,134,673 | 11,646,394 | (511,721) |

ሠንጠረዥ 3/ለ **የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የ1994 በጀት አጠቃቀም**

| የሂሣብ መደብ | ለ1994 በጀት ዓመት ከመንግስት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመት ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት 03 እና 04 |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| 6113 | 827,000 | 827,000 | 941,500 | (-114,500) |
| 6114 | 37,700 | 37,700 | 51,600 | (-13,900) |
| 6123 | 43,200 | 43,200 | 60,900 | (-17,700) |
| 6212 | 20,000 | 20,000 | 38,800 | (-18,800) |
| 6213 | 200,000 | 200,000 | - | 200,000 |
| 6217 | 533,000 | 533,000 | 313,500 | 219,500 |
| 6231 | 485,600 | 485,600 | 429,800 | 55,800 |
| 6232 | 70,000 | 70,000 | 15,800 | 54,200 |
| 6241 | 519,200 | 519,200 | 296,900 | 222,300 |
| 6243 | 60,000 | 60,000 | 2,800 | 57,200 |
| 6252 | 205,000 | 205,000 | 226,400 | (21,400) |
| 6254 | 43,600 | - | - | - |
| 6257 | 26,400 | 26,400 | 29,200 | (2,800) |
| 6258 | 200,000 | 200,000 | 116,900 | 83,100 |
| 6259 | 13,200 | 13,200 | 8,500 | 4,700 |
| 6271 | 100,000 | 100,000 | 99,800 | 200 |
| | 3,383,900 | 3,340,300 | 2,632,400 | 707,900 |

ሠንጠረዥ 3/ሐ  የግብርና ናሙና ቆጠራ የ1994 በጀት አጠቃቀም

| የሒሳብ መደብ | ለ1994 በጀት ዓመት ከመንግስት ግምጃ ቤት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመት ከተፈቀደው ውስጥ ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነ | በእጅ ከገባው ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ | ልዩነት 03 እና 04 |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| 6113 | 47,666,650 | 47,666,650 | 49,266,224 | (1,599,574) |
| 6114 | 10,802,495 | 10,802,495 | 7,144,667 | 3,657,828 |
| 6123 | 3,570,684 | 3,570,684 | 3,036,435 | 534,249 |
| 6212 | 2,269,555 | 2,269,555 | 2,103,343 | 166,212 |
| 6217 | 5,800,816 | 5,800,816 | 3,088,477 | 2,712,339 |
| 6231 | 46,282,400 | 46,282,400 | 50,864,971 | (4,582,571) |
| 6232 | 3,995,698 | 3,995,698 | 3,822,214 | 173,484 |
| 6241 | 6,200,000 | 6,200,000 | 7,273,843 | (1,073,843) |
| 6243 | 50,000 | 50,000 | 16,214 | 33,786 |
| 6252 | 755,920 | 755,920 | 242,948 | 512,972 |
| 6253 | 200,000 | 200,000 | 196,754 | 3,245 |
| 6254 | 3,006,582 | 2,991,582 | 2,783,140 | 208,442 |
| 6255 | 283,333 | 283,333 | 164,340 | 118,993 |
| 6257 | 36,000 | 36,000 | 51,337 | (15,336) |
| 6258 | 660,000 | 660,000 | 372,223 | 287,777 |
| 6259 | 252,667 | 252,667 | 186,376 | 66,291 |
| 6314 | 145,000 | 145,000 | 194,198 | (49,198) |
| | 131,980,800 | 131,965,800 | 130,807,703 | 1,158,097 |

## 14. አገልግሎት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

በባለሥልጣኑ መ/ቤት ያሉት የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በበጀት ዓመቱ ውስጥ በዕቅድ ለተያዙት በሁለት ፕሮጀክቶች ስር ላሉ ጥናቶች እገዛ የሚያደርጉ ሥራዎችን አከናውነዋል:: ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል::

### 14.1 የዕቃ ግዥን በተመለከተ

ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ድረስ ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶች አገልግሎት እንዲውሉ በመንግሥት በጀት ብር 18,737,375.05 የሚያወጣ የተለያዩ ግዥዎች ተፈፅመዋል:: ዝርዝሩም በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል::

ሠንጠረዥ 4 በ1994 በጀት ዓመት ውስጥ የተፈፀመ የአገልግሎት፣ የሥራና የዕቃ ግዥ

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት /የአገልግሎቱ ዓይነት | የገንዘብ መጠን | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ሣ |
| 1 | የኮምፒውተር ዕቃዎች፣ ፕሪንተሮችና ተዛማጁ ዕቃዎች | 739,381 | 00 |
| 2 | የጽሕፈት መሣሪያ | 1,856,010 | 36 |
| 3 | ለግብርና ቆጠራ የተገዙ ዕቃዎች(በጥቅል) | 1,060,290 | 00 |
| 4 | ለግብርና ቆጠራ መጠይቅና ፖስተር የታተመበት | 424,366 | 75 |
| 5 | የተለያዩ የጥገናና የኤሌክትሪክ ዕቃዎች | 261,016 | 05 |
| 6 | በዕርዳታና በመንግሥት ለተገዙ ዕቃዎች የቀረጥ፣ ለኪራይና ዲክላራሲዮን (ለቀረጥ የወጣው ወጪ በገንዘብ ሚ/ር በኩል የተከለፈለ ነው) | 9,779,312 | 25 |
| 7 | ለማስታወቂያና ለጋዜጦች ግዢ | 26,967 | 10 |
| 8 | ልዩ ልዩ ወጪዎች (ቲተርና ማኅተም፣ የፅዳት ዕቃዎች...ወዘተ) | 445,581 | 21 |
| 9 | የቆጠራ ዶክመንት ለማንንዝ የተከፈለ | 82,709 | 00 |
| 10 | የተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች | 286,549 | 11 |
| 11 | የደንብ ልብስ፣ መጋረጃና የቢሮ ምንጣፎች | 243,798 | 22 |
| 12 | ለነዳጅና ቅባት | 3,164,886 | 75 |
| | ድምር | 18,737,375 | 05 |

## 14.2 ትራንስፖርትና ጥገና

- በመንግሥት በጀት ለኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ የተገዙ 3ቱ በUNFPA እና በUSAID ለስነ ህዝብና ጤና ጥናት 9 የመስክ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በUSAID ለቆጠራ ሥራው በዕርዳታ ለተገዙት 60 ፎርድ ሬንጀር የመስክ ተሽከርካሪዎች በድምሩ ለ101 መኪኖች የቴክኒክ ምርመራና ውሌዳ በማውጣት ለቆጠራው አገልግሎት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

- 175 የመስክና ለመ/ቤቱ የሰርቪስ አገልገሎት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ተደርጎላቸዋል፡፡

- 406 የመስክ ተሽከርካሪዎች (አንድ ተሽከርካሪ ከሁለት ጊዜ በላይ) ከባድና መለስተኛ ጥገናዎች እንዲሁም ሰርቪስ በዋናው መ/ቤት ተደርጎላቸው ለሥራ የተሰማሩ ሲሆን፣ ለእነዚህም ተሽከርካሪዎች በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለጥገናና ለጎማ ግዢ በጠቅላላው ብር 7,578,711 ወጪ ሆኗል:: እንዲሁም ሌሎች 10 ተሽከርካሪዎች በመ/ቤቱ ወጪ በጋራዥ ጥገና ላይ ናቸው::

- 67 የመስክ ተሽከርካሪዎች (አንድ ከሁለት ጊዜ በላይ ) የመድን ሽፋን ስለነበራቸው ተጠግነው ወደ ሥራ የተሰማሩ ሲሆን፣ እንዲሁም ሌሎች 10 ተሽከርካሪዎች በመድህን ሽፋን ጥገና ላይ ይገኛሉ፡፡

- ለዋናው መ/ቤት በበጀት ዓመቱ በሰርቪስ አገልግሎት ላይ 27 ተሽከርካሪዎች እንዲሰማሩ ተደርጓል::

- 34 የመስክ ተሽከርካሪዎች በከፍተኛ ብልሽት ምክንያት በአገር ውስጥ መለዋወጫ ዕቃቸው ባለመገኘቱና የመጠገኛ ዋጋቸውም ከፍተኛ በመሆኑ ከአገልግሎት ውጭ ተደርገው ቆመዋል፡፡

## 14.3 የሕትመት ዋና ክፍል

የመ/ቤቱ የሕትመት ዋና ክፍል ከሐምሌ 1 ቀን 1993 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1994 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 295,736 የተለያዩ ዓይነት ጥራዞች፣ በጠቅላላው 20,925,915 ገጽ ያላቸው ሕትመቶች አትሞ ለሚመለከተው ክፍል ያቀረበ ሲሆን፣ ከተለያዩ ክፍሎች ለሚቀርቡለት የፎቶ ኮፒ አገልግሎት ሰጥቷል::

## 15. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ሀ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሥራ ስፋት በየዓመቱ እየጨመረ በመሄዱ በርካታ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች ቀጥሮ በማሠራት ላይ ይገኛል:: መንግሥት ለመ/ቤቱ በሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ለወደፊቱ የሚጠኑ ጥናቶችን ለማስፈፀም እንዲቻል ተጨማሪ የሰው ኃይል ቅጥር እንደሚኖር ካለፉት የመ/ቤቱ ተሞክሮዎች ለመገንዘብ ይቻላል:: ሆኖም መ/ቤቱ በየወቅቱ በሚያቀርባቸው ሪፖርቶችና የበጀት ፍላጎት ጥያቄ ላይ አሁን ያሉት ቢሮዎች ያለውን የሰው ኃይልና በተለያዩ ጊዜያቶች በተጠኑ ጥናቶች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በቂ ቢሮዎችና መጋዘኖች እንደሚያስፈልጉ ቢጠየቅም ማሟላት አልተቻለም:: በመሆኑም በከፍተኛ የሃገር ሃብት የተማሩ ባለሙያዎች ተስማሚ የሆነ የሥራ ቦታ ባለማግኘታቸው የዕለት ተዕለት ሥራቸውን ለማከናወን ችግር ፈጥሮባቸዋል:: ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ችግሩን ለበላይ አካል በማሳወቅ ግንባታ ለማካሄድ እንዲችል ጥያቄ ቢያቀርብም ለግንባታ የሚሆን ቦታ ለማግኘት በአዲስ አበባ መስተዳድር በኩል ቀና ምላሽ አላገኘም:: ስለዚህ ለዘለቄታው ችግሩን ለመፍታት እንዲቻል አስቸኳይ መፍትሄ እንዲሰጥበት ያስፈልጋል፡፡

ለ. የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚያካሂዳቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሕዝብ ነክ ጥናቶች ከፍተኛ የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚጠይቁ በመሆናቸው መ/ቤቱ በየጊዜው ያሉትን ባለሙያዎች ለከፍተኛ ትምህርትና የተለያዩ ዓለማቀፋዊ ሴሚናሮች፣ አውደ ጥናቶችና የምርምር ሪፖርቶች በሚቀርቡበት ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ በማድረግ ያላቸው ልምድ የሚያካፍሉበትንና ተጨማሪ ተሞክሮዎች የሚያገኙበትን ሁኔታ እያመቻቸላቸው ይገኛል:: ሆኖም ለእነዚህ ባለሙያዎች አሁን የሚከፈላቸው ደመወዝ በተመሳሳይ ደረጃና ሙያ ካላቸው ሌሎች ድርጅቶች ከሚሠሩ ባለሙያዎች ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ለተሻለ ክፍያ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎቹ መ/ቤቱን እየለቀቁ ይገኛሉ:: ስለዚህ መንግስት ይህንን ችግር ለዘለቄታው መፍታት እንዲቻል ለመ/ቤቱ ልዩ የደመወዝ ስኬል እንዲፈቀድ እንጠይቃለን፡፡

ሐ. ባለሥልጣኑ መ/ቤት አሁን ባለው አወቃቀር በተወሰኑ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ላይ አስፈላጊ ያልሆነ የሥራ ጫና የተፈጠረ በመሆኑ በተለይም 22 ቅ/ጽ/ቤቶችን በአንድ መምሪያ ከዋናው መ/ቤት ለመቆጣጠርና ለመምራት አስቸጋሪ ሆኗል:: በተጨማሪም የሕዝብ ጥናት ማዕከል የነበረውና በም/ዋና ሥራ አስኪያጅ ደረጃ ሲመራ የነበረው አካል ከሐምሌ 1 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 180/1991 ዓ.ም ራሱን ችሎ በሕዝብ ተወካዬች ም/ቤት ሥር የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን

ጽ/ቤት በሚል እንዲተዳደር ሆኗል። ስለዚህ በማዕከሉ ሥር የነበሩት መምሪያዎች በሙሉ እንዲሁም በባለሥልጣኑ መ/ቤት ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው የተወሰኑ አባላት (በተለይም የካርቶግራፊ ኤክስፐርት ቡድን) ወደ ኮሚሽኑ ጽ/ቤት እንዲዛወር ተደርጓል:: በመሆኑም የባለሥልጣኑን መ/ቤት በአዲስ መልክ ማደራጀት ያስፈልጋል::

ስለዚህ የማህበራዊ ስታቲስቲክስ መረጃን በተመለከተ በኃላፊነት የሚሰራው መምሪያ እንደዚሁም 22ቱን ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያስተባብረው የአካባቢ ጽ/ቤቶችና የመስክ ሥራ ከነውን መምሪያ ጋር በቅንጅት የማስተባበር ተግባር የሚፈፅም ተጨማሪ አንድ ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ መመደብ ያስፈልጋል:: በመሆኑም ይህ ተግባር የመ/ቤቱን መዋቅር በመጠኑም ቢሆን ማሻሻል የሚያስፈልግ መሆኑን ተገንዝበናል:: ስለዚህ የመ/ቤቱን መዋቅር መጠነኛ ማሻሻል ለማድረግ እንዲቻል ከዚህ ቀደም ሲሰራበት የነበረውን መዋቅርና የመ/ቤቱን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና የሚወስን አዋጅ አዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ከወዲሁ እንዲፈቀድ እንጠይቃለን::